# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## የአርብ ፕሮግራም

በአርብ **ፕሮግራም** እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ አሁን ወንድም ሲሳይ "የእግዚአብሔር መንግስት" በሚል ርእስ ተከታታይ ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛል። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ ከዚያ አለ።" (መዝ. 50:23)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **December 2, 2018** | **ሕዳር 16፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእሁድ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. ወንድም ረድኤቱ ግርማ ካሳ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወንድም ሲሳይ መሸሻ

ቃል ............. ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ:- ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።" (ራዕ. 4:10-11)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### አመስጋኙ ሳምራዊ።

በሉቃስ 17 ላይ አስገራሚ ታሪክ እናነባለን። ጌታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በገሊላና በሰማሪያ መካከል አለፈ. (ቁ. 11)። ወደ አንዲት መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙ አስር ለምጻሞች ተገናኙት። እዚህ ጋ ልብ የምንለው በብሉይ ኪዳን ስርዓት በለምጽ የተመታ ሰው እንደ እርኩስ ስለሚቆጠር ከለምጹ እስኪነጻ ድረስ ከማህበረሰቡ ተለይቶ ነበር የሚኖረው። ለዚህም ይመስላል እነኚህ አስር ለምጻሞች ወደ ጌታ ሳይቀርቡ በርቀት የቆሙት። ለምጻሞቹ ወደ ጌታ ለመቅረብ አልደፈሩም ነገር ግን በሩቅ ቆመው "ኢየሱስ ሆይ፥ አቤቱ ማረን" እያሉ ጮሁ። ችግረኞችን አይቶ የማያልፈው ጌታ ወደ እነርሱ ተመለከተ። "ሂዱ ራሳችሁን" ለካህናት አሳዩ" አላቸው። ለምጻሞቹም ቃሉን ይዘው እንደ ስረዓቱ ራሳቸውን ለካህናት ለማሳየየት ሲሄዱ ሳለ ነጹ። የነጹት አስሩም ናቸው። ነገር ግን መፈወሱን አይቶ ለምስጋና የተመለሰው አንዱ ብቻ ነበር። ለማመስገን ስለተመለሰው አንዱ ቃሉ ሲናገር "ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፥ እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ" (ቁ. 15-16) ይለናል። ይህ ሳምራዊ ከፈውሱ በላይ የፈወሰውን ጌታ አከበረ። ዘጠኙ ግን የፈለጉት ጌታን ሳይሆን ፈውሳቸውን ብቻ ነበር። ጌታ የተደነቀው ሊያመሰግን በተመለሰው ሳይሆን ፈውሳቸውን ይዘው ለምስጋና ባልተገኙት ዘጠኙ ነበር። ጌታ እንዲህ ጠየቀ፡ "አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ" (ቁ. 17-18)። ሊያመሰግን የተመለሰው ሳምራዊ የስጋን ፈውስ ብቻ ሳይሆን የነፍስ መዳንም እንደሆነለት ከቃሉ እናነባለን። ጌታ ሳምራዊውን አመስጋኝ "ተነሳና ሂድ እምነትህ አድኖሃል" አለው (ቁ. 19)። ለሳምራዊው በእምነት የሆነለት መዳን ከስጋው ፈውስ ያለፈ ነበር።

እኛም ከአመስጋኙ ሳምራዊ የምንማራቸው ብዙ ቁብ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ:- ይህ ሰው የተደነቀው በፈውሱ ሳይሆን በፈወሰው ጌታ ነበርና ለማመስገን ተመለሰ። እኛም ከተደረገልን ይልቅ ያደረገልን ጌታ ላይ አይናችን ሲያርፍ በምንም ሁኔታ አመስጋኞች እንሆናለን። ሁለተኛ:- ምስጋናው ያልተቆጠበ ነበር። በታላቅ ድምጽ፣ አለ ይሉኝታ ነበር እግዚአብሔርን ያመሰገነው። "ለምጻም ነበርኩ። እግዚአብሔር ፈወሰኝ። እግዚአብሔር ይመስገን። ከሰው የቀላቀለኝ አምላክ ይባረክ" እያለ ጮኸ። ይህም ሳይበቃው በጌታ እግር ፊት በግንባሩ ወድቆ ሰገደ። እኛም በሙሉ ኃይላችን ስለተደረግልን ሁሉ ሳንቆጥም የምናመሰግን መሆን ይገባናል። ሶስተኛ:- የምስጋናው ኃይል ጌታን አንቀሳቀሰው። ሰውዬው በምስጋናው ውስጥ እምነቱን ገለጸ፤ ፈውሱ ወደ እምነት አመጣው። በስጋው ፈውስ ተደንቆ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን የዘላለም ደህንነትንም አገኘ። እግዚአብሔር ይመስገን። እኛም በምስጋና ስንሞላና እግዚአብሔርን ስናመሰግን ከድል ወደ ድል እንሻገራለን። ቃሉም እንደሚለን የምስጋና መስዋዕትን የሚሰዋ እግዚአብሔርን ያከብራል። በዛም ውስጥ የሚበልጠውን የግዚአብሔርን ማዳን ያያል። (መዝ. 50:23) አመስጋኞች እንሁን።